ቁጥር OFAGF-03.16/ም/39
ቀን 29/03/2015

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለተከበሩ አቶ አህመድ ሺዴ

የገንዘብ ሚኒስትር

<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ውጤትና አስተያየትን ይመለከታል</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የገለሠራጣን የኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 13 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 12 ገጽ የሂሣብ ሪፖርቶች በድምሩ 25 ገጽ የያዘ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እየገለጽን ለኦዲት ግኝቶች የድርጊት መርሃ ግብር በማዘጋጀት እንድትልኩልን እናሳስባለን፡፡

ከማክበር ሠላምታ ጋር

ጌታሁን ዳምጤ
የፋይናንሺና ኮምፕሊያንስ መስ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን
  (ከ13 ገጽ የኦዲት ሪፖርት ፣12 ገጽ የሂሳብ ሪፖርቶች
  እንዲሁም 46 ገጽ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች የያዘ የሥራ አመራር
  ሪፖርት እና 1 ገጽ የድርጊት መርሃ ግብር)
  <u>አዲስ አበባ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

የኦዲት ሪፖርት

ህዳር/2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የተመደበለትን የመደበኛና የካፒታል ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የባለስልጣኑ ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል:: ኦዲታችን :-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል::

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል::

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ባለስልጣኑ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው:: ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች (Basics of Audit Opinion)

የባለስልጣኑ የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

1. በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ፣

የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ሁለት የመደበኛና ካፒታል የስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈጸም ወጪው ለሚደረግበት ተግባር በበጀት ዓመቱ የተያዘ ወይም ወጪውን ለመሸፈን ቀሪ በጀት መኖሩን እና ወጪው በመስሪያ ቤቱ ዕቅድ ውስጥ የተያዘና በጥሬ ገንዘብ ፍላጎት ላይ የተካተተ መሆኑ ሳይረጋገጥ ወጪ መፈጸም እንደማይገባ መመሪያው ይገልጻል፡፡ አስተዳደሩ ክፍያዎችን በወቅቱ እየፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ወጪዎች ናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ በድምሩ ብር 86,923.20 በ2013 በጀት ዓመት ተገዝቶ አገልግሎት ላይ የዋለ ነዳጅ የበጀት ዓመቱን ክፍያ በበጀት ዓመቱ ውስጥ መክፈልና ማወራረድ ሲገባው ወይም በ2014 በጀት ተይዞ እንደሚከፈል በተከፋይ ሂሳብ ሳይያዝ ያለበጀት ዓመቱ በ2014 በጀት ዓመት ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2. የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ የተፈጸመ ክፍያን በተመለከተ፣

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ የመደበኛ ስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈፀሙ መሟላት አለባቸው ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ በተ/ቁጥር 4 ላይ ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መሟላት እንዳለባቸው እና በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ኦሪጅናል ደረሰኝ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት መስራቱን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ በድምሩ ብር 607,740.61 ክፍያ ውል የሌለው፣ የሰልጣኞቹ ዝርዝርና የሰልጣኞች አቴዳንስና፣ የቀረበው ደጋፊ ማስረጃ ቀን ትክክል አለመሆኑ እና

ለነዳጅ ወጪዎች ደጋፊ ማስረጃዎች ሳይሟሉ ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ የወጪውን ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ክፍያ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>ዝቅተኛ ዋጋ አቅራቢውን በመሰረዝ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት የተፈጸመ ግዥ፣</u>

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 6 ተቀራራቢ የጥራት ደረጃ ያላቸዉና በመ/ቤቱ የሚፈለገዉን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበዉን ተጫራች አሸናፊ አድርጎ መምረጥ ያስፈልጋል ይላል፡፡ ባለስልጣኑ በመመሪያ መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ:-

ባለስልጣን መ/ቤቱ የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ የሚያሟሉ አቅርቦቶችን በማወዳደር ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበዉን ተጫራች አሸናፊ አድርጎ መምረጥ ሲገባው ዝቅተኛ የመወዳደሪያ ዋጋ ባቀረበው ድርጅት የዋጋ ማቅረቢያ (ፕሮፎርማ) ላይ በመሰረዝ እና ብር በመጨመር ከፍተኛ ዋጋ እንዳቀረበ በማድረግ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ ድርጅት ግዥ የተከናወነ ሲሆን በድምር ብር 24,934.50 ያለአግባብ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>መደበኛ ሚዛኑን ያልጠበቀ የተጠራ ሀብት፣</u>

በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 2(ለ) እና (ሐ) እንዲሁም ተራ ቁጥር 6(መ) መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን (ዴቢት ወይም ክሬዲት) ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ መመሪያው ተግባራዊ መደረጉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የባለስልጣን መ/ቤት የ2014 በጀት ዓመት የተጣራ ሀብት (Net asset equity) በሂሳብ መደብ 5601(7111101) ብር 1,099,359.67 ከመደበኛ የሂሳብ ሚዛን ውጭ በዴቢት የታየ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፣

ከላይ ከተራ ቁጥር 1-4 ከተመለከቱት ሁኔታዎች በስተቀር የመንግስት ግዥና ንብረት ባለስልጣን የ2014 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የተፈጸመ በመሆኑ እንዲሁም የሂሳብ ሪፖርቶቹ በሂሳብ አያያዝ ማእቀፍ መሰረት የተዘጋጁ በመሆናቸው በእኛ አስተያየት አጥጋቢ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል።

<u>ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች(Emphasis matter)</u>

1. <u>የክፍያ መመሪያ ያልተከተሉ ወጪዎች፣</u>

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል አንድ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃዉ ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረቡን ማረጋገጥ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ በመመሪያው መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 1,493,356.67 ለተከናወኑ የዕቃ ግዥ፣ ዕቃው ወደ መ/ቤቱ ዕቃ መጋዘን ገቢ ሳይደረግ ወይም የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል-19) ሳይቀረጥ አስቀድሞ ክፍያዎች የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

1.1 <u>ከፕሮጀክት ሂሳብ ያለ አግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ክፍያ</u>

1.1.1 <u>ከፕሮጀክቱ ዓላማ ውጭ የተከፈለ የውሎ አበል እና የነዳጅ ክፍያ፣</u>

ገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 24/02/13 ቁጥር የ.ተ.መ.2/16/670 በተለያዩ የልማት አጋሮች ድጋፍ በመካሄድ ላይ የሚገኙ ፕሮግራሞች /ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየውን የተለያየ የውሎ አበል አከፋፈል ተመን የገንዘብ ሚኒስቴር ከልማት አጋሮች ቡድን ጋር በመወያየት ወጥ እንዲሆን በማድረግ በ2013 ዓ/ም በወጣው መመሪያ ካለው የገበያ ሁኔታ ጋር ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች አንፃር በመቃኘት ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ ይህ መመሪያ በሁሉም የልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚተገበሩ ፕሮግራሞች /ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በፌደራልና በክልል በሚዘጋጁ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮች፣

ኮንፈረንሶች፣ ዓውደ-ጥናቶች፣ ስልጠናዎች፣ የመስክ ክትትልና ግምገማዎች፣ የማህበረሰብ-አቀፍ ንቅናቄዎች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ስራዎች ሲዘጋጁ ለሚገኙ ተሳታፊዎች የውሎ አበል እና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎችን አከፋፈልና መጠን ይገልጻል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ የፕሮጀክት ሂሳብ የውሎ አበል ክፍያዎችን በመመሪያ መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ መደበኛ ስራ ለሆኑ ለኦዲት ስራ እና ህንጻ እርክክብ ለማድረግ ሀዋሳ ለሄዱ ሰዎች ውሎ አበል እና ነዳጅ በድምሩ ብር 35,832.16 ያለአግባብ ከፕሮጀክቱ ዓላማ ውጭ ክፍያ ፈፅሞ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፣

1.1.2 ከተመን በላይ ከፕሮጀክት የተከፈለ ውሎ አበል

ገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 24/02/13 ቁጥር የ.ተ.መ.2/16/670 በተለያዩ የልማት አጋሮች ድጋፍ በመካሄድ ላይ የሚገኙ ፕሮግራሞች /ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየውን የተለያየ የውሎ አበል አከፋፈል ተመን የገንዘብ ሚኒስቴር ከልማት አጋሮች ቡድን ጋር በመወያየት ወጥ እንዲሆን በማድረግ በ2013 ዓ/ም በወጣው መመሪያ ካለው የገበያ ሁኔታ ጋር ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች አንፃር በመቃኘት ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ ይህ መመሪያ በሁሉም የልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚተገበሩ ፕሮግራሞች /ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በፌደራልና በክልል በሚዘጋጁ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮች፣ ኮንፈረንሶች፣ ዓውደ-ጥናቶች፣ ስልጠናዎች፣ የመስክ ክትትልና ግምገማዎች፣ የማህበረሰብ-አቀፍ ንቅናቄዎች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ስራዎች ሲዘጋጁ ለሚገኙ ተሳታፊዎች የውሎ አበል እና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎችን አከፋፈልና መጠን የሚገልፅ ነው፡፡ በተጨማሪም ንዑስ አንቀፅ 2.4.3 የመንግስት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በወረዳ ዋና ከተሞች ላይ ለሚደረጉ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ በአዲሱ የሲቪል ሰርቪስ የውሎ አበል አፈፃጸም መመሪያ አንቀፅ 3 ተራ-ቁጥር 2 እና 3 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ደሞዝ እና የስራ ደረጃን መሰረት በማድረግ ልዩነት ሳይደረግ በቀን ብር 450.00 የውሎ አበል እንደሚከፈል ይገልፃል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ባለስልጠን መስሪያ ቤቱ ስራዎችን ማከናወኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች እና ከተለያዩ የፌደራል መስሪያ ቤቶች ለመጡ ሠራተኞች በቢሾፍቱ ከተማ በተለያየ ጊዜ ለተሰጡ የተለያዩ ስልጠናዎችን

የውሎ አበል በቀን ብር 450.00 መከፈል ሲገባው ያለአግባብ ከተመን በላይ ብር 650.00 በመክፈል በድምሩ ብር 651,000.00 በብልጫ ክፍያ የፈፀመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፣

1.1.3 <u>መከፈል ከነበረበት ቀናት በላይ የተከፈለ</u>

ገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 24/02/13 ቁጥር የ.ተ.መ.2/16/670 በተለያዩ የልማት አጋሮች ድጋፍ በመካሄድ ላይ የሚገኙ ፕሮግራሞች /ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየውን የተለያየ የውሎ አበል አከፋፈል ተመን የገንዘብ ሚኒስቴር ከልማት አጋሮች ቡድን ጋር በመወያየት ወጥ እንዲሆን በማድረግ በ2013 ዓ/ም የወጣውን መመሪያ ካለው የገበያ ሁኔታ ጋር ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች አንፃር በመቃኘት ማሻሻያ ተደርጓዋል፡፡ይህ መመሪያ በሁሉም የልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚተገበሩ ፕሮግራሞች /ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ በፌደራልና በክልል በሚዘጋጁ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮች፣ ኮንፈረንሶች፣ ዓውደ-ጥናቶች፣ ስልጠናዎች፣ የመስክ ክትትልና ግምገማዎች፣ የማህበረሰብ-አቀፍ ንቅናቄዎች እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ስራዎች ሲዘጋጁ ለሚገኙ ተሳታዎች የውሎ አበል እና ሌሎች ተዛማጅ ወጪዎችን አከፋፈልና መጠን የሚገልፅ ነው፡፡ በተጨማሪም ንዑስ አንቀፅ 2.4.2 የመንግስት ሠራተኞች እና ሌሎች ባለ ድርሻ አካላት በክልልና በዞን ዋና ከተሞች በሚደረጉ ክንውኖች ላይ ሲሳተፉ በአዲሱ የሲቪል ሰርቪስ የውሎ አበል አፈፃጸም መመሪያ አንቀፅ 3 ተራ-ቁጥር 2 እና 3 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ደሞዝ እና የስራ ደረጃን መሰርት በማድረግ ልዩነት ሳይደረግ በቀን ብር 650 የውሎ አበል እንደሚከፈል ይገልፃል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ባለስልጠን መስሪያ ቤቱ ስራዎችን መስራቱን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ በድምር ብር 62,400.00 ያለአግባብ መከፈል ከነበረበት ቀናት በላይ የውሎ አበል ክፍያ ፈፅሞ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፣

1.1.4 <u>ሙሉ ወጪ ተሸፍኖ በተጨማሪ የተከፈለ ውሎ አበል፣</u>

የፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ገንዘብ ሚኒስቴር በቀን 24/02/13 ቁጥር የ.ተ.መ.2/16/670 በልማት አጋሮች ድጋፍ ለሚተገበሩ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የወጣ የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ አንቀፅ 2.2 ለውሎ አበል ብቁ የሚያደርጉ ሁኔታዎች የመንግስት ሰራተኞች እና ወይም ሌሎች ባለድርሻ አካላት እና ወይም

የማህበረሰብ አባላት ተሳታፊ በልማት አጋሮች ድጋፍ ከሚካሄዱ ፕሮግራሞች/ፕሮጀክቶች የተለያዩ ክንውኖች ጋር በተየያዘ ለስራ ተሰማርቶ ዕለቱን ወደ መኖሪያው መመለስ ካልቻለ ለእያንዳንዱ በመስክ ስራ ለቆየበት ቀን የውሎ አበል ወጪውን ለመሸፈን በአዲሱ የሲቪል ሰርቪስ የውሎ አበል አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 3ተራ ቁጥር 2 እና 3 መሰረት የውሎ አበል ለማግኘት ብቁ በማለት ይገልጻል፡፡ ባለስልጠን መስሪያ ቤቱ የፕሮጀክት ሂሳብ ውሎ አበል ክፍያ በመመሪያው መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

ባለስልጣን መ/ቤቱ በድምሩ ብር 47,450.00 ሙሉ ወጪ ተሸፍኖ እያለ ያለአግባብ ከመመሪያ ውጭ በተጨማሪ የውሎ አበል ክፍያ የተፈጽመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. <u>ከስልጣን ገደብ በላይ የተፈቀደ የወጪ ሂሳብ፣</u>

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 የመንግስት የሒሳብ አያያዝ ዝርዝር አፈጻጸም ንዑስ ክፍል 8 ተራ ቁጥር 2ለ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ በመመሪያ መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ የወጪ ሂሳብ በናሙና ኦዲት ሲደረግ:-

ባለስልጣን መ/ቤቱ መደበኛ የስራ በጀት ከተመደበው በአንድ ጊዜ ትዕዛዝ የፋይናንስ ግዥና ንብረት ዳይሬክተር እስከ 100,000.00፣ የቼክና ወጪ አድርጎ እንዲከፈል፣ የመወሰንና የመፈረም ከሚመለከተው አካል ውክልና የተሰጣቸው ቢሆንም በድምሩ ብር 11,317,661.69 እንዲፈርሙ ከተሰጣቸው የስልጣን ገደብ በላይ ወጪውን በማጽደቅ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

4. <u>በወቅቱ ያልተወራረዱ ተሰብሳቢ፣</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ፤ በመመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ደግሞ ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት የዘረዘ ይሁንና

ባለስልጣን መ/ቤቱ ተሰብሳቢ ሂሳቦችን በደንቡና በመመሪያው መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚያደርግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

ባለስልጣን መ/ቤቱ ከተለያዩ ግለሰቦች እና ድርጅቶች የሚፈለግ ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተሰብስቦ በወቅቱ ሂሳቡ መወራረድ ሲገባው የኦዲት ስራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ በድምሩ ብር 1,155,209.50 በወቅቱ ያልተወራረደ በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይ መሆኑን፣

5. **<u>በወቅቱ ያልተወራረዱ የተከፋይ ሂሳብ</u>**

በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 8/5/ሀ ማናቸውም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንደሚገባቸው ያዛል፡፡ በዚህ መመሪያ መሰረት ባለስልጣን መ/ቤቱን የተከፋይ ሂሳብ መስራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

ባለስልጣን መ/ቤቱ በድምሩ ብር 494,579.53 በወቅቱ ተከፍሎ ማወራረድ ሲገባው ሳይወራረድ ውዝፍ በተከፋይ ሂሳብ የሚታይ መሆኑን፣

6. **<u>ስራ ላይ ያልዋለ በጀት በተመለከተ፣</u>**

የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል ሶስት አንቀፅ 12 ተራ ቁጥር 1 ማንኛውም የመንግስት መስሪያ ቤት ለበጀት አመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛና የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠር እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ባለስልጣን መ/ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙን በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል በ2014 በጀት ዓመት ለባለስልጣን መ/ቤቱ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ የመደበኛ በጀት በየፕሮግራሙ ከ10% (በመቶ) በላይ ያልተሰራበት በጀት መኖሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ የበጀት አስተዳደር ከሐምሌ/2013 እስከ ሰኔ 30/2014 የተስተካከለ በጀት በየሂሳብ አርዕሶቹ በትክክለኛ ከወጣው ወጪ ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 1,450,073.71 ስራ ላይ ያልዋለ መሆኑን፣

__ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)__

1. __የቋሚ እና አላቂ እቃ አያያዝና አጠባበቅን በተመለከተ፣__

የባለስልጣን መ/ቤቱ የንብረት አመዘጋገብ፣ አያያዝ፣ አጠባበቅ እና አወጋገድ በፌደራል መንግስት የንበረት አስተዳደር መመሪያ ቀጥር 9/2003ዓ.ም አንቀጽ 5 መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

- የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል-19) እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል-22) የሚያዘውና የሚዘጋጀው በአንድ ሰራተኛ መሆኑን፣
- አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ቁጥራቸው 21 የተለያዩ የፕሪንተር ቀለሞች ከሶስት ዓመት በላይ ያለአገልግሎት በንብረት ክፍል ውስጥ የተቀመጡ መሆኑን፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ብዛታቸው ከ300 በላይ የሆኑ የፕሪንተር ቀለሞች ሳይወገዱ በንብረት ክፍል ተከማችተው የሚገኝ መሆኑን፣
- ብዛታቸው ሶስት (3) የሆኑ 65 ኢንች እና ሁለቱ ኢንቻቸው የማይታወቅ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረት ክፍል ውስጥ ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኝ መሆኑን፣
- አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ብዛታቸው አስር (10) ኮፒዩተር ከነተጓዳኙ ንብረት ክፍል የሚገኝ መሆኑን፣
- የ2014 በጀት ዓመት የንብረት ቆጠራ ሪፖርት ለኦዲት ሥራ ያልቀረበ መሆኑን፣
- የዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ዘጠኝ (9) ላፕቶፕ፣ አስራ ሶስት (13) ዴስክ ቶፕ ኮፒዩተር ፣ ሰማንያ ሰባት (87) USP፣ ሰላሳ አንድ (31) ፕሪንተር፣ ሁለት (2) ፋክስ ማሽን፣ ሁለት(2) የላፕቶፕ ቻርጀር፣ ሁለት(2) ስዊች፣ ሀለት(2) ፎቶ ኮፒ ማሽን እና አንድ መቶ አስራምስት (115) የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ሳይወገዱ በግምጃ ቤቱ የሚገኙ መሆኑን፣
- ብዛታቸው ሁለት የሆኑ ሞተሮች ከሶስት (3) አመት በላይ ያለአገልግሎት ንብረት ክፍል የሚገኙ መሆኑን፣

የህግ ጉዳዮች በተመለከተ(Compliance Issue)

1. የእጅ በእጅ ሽያጪ ደረሰኝ የተወራረደ ሂሳብ፣

የፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት ስለመንግስት ገንዘብ ክፍያ የመደበኛ ስራ ማስኬጃ ወጪዎች ሲፈፀሙ መሟላት አለባቸው ብሎ ከዘረዘራቸው ውስጥ በቁጥር 4 ላይ ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መሟላት አለባቸው ይላል፡፡ ባለስልጣኑ የሚያወጣቸው ወጪዎች የተፈጸሙት በተሟላ ሰነድ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

ባለስልጣን መ/ቤቱ ከመደበኛ በጀት ብር 1,472,924.26 እና ከፕሮጀክት ብር 4,600,899.84 በድምሩ ብር 6,073,824.10 ገንዘቡን ስለመቀበሉ ህጋዊ የሆነ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ (ካሽ ሪጅስተር ደረሰኝ) በመቀበል ክፍያ መፈጸም ሲገባው የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ተወራርዶ የተገኘ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

2. የገበያ የዋጋ ጥናት ሳያካሄድ የተፈጸመ ግዥ፣

ሰኔ 2002 ዓ.ም በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻፀም መምሪያ ክፍል ሁለት አንቀፅ 8 ንኡስ አንቀፅ 24(8) መ/ቤቱ በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈፅማቸው ግዥዎች በኤጀንሲው ድህረ ገፅ የሚያወጣውን ወቅታዊ የዋጋ ዝርዝር እና በግዥ ስራ ክፍሉ የሚካሄድ የገበያ ጥናት በመጠቀም ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ማመን እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ባለስልጣኑ በመመሪያ መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ:-

ባለስልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ ቀናት የተለያዩ ዕቃዎችን በተደጋጋሚ በዋጋ ማቅረብያ ግዥ ዘዴ ሲፈፅም በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት ሳይደረግ፣ በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ከሚወጣው ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር ሳይመሳከር እና ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛና ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መሆኑን ሳያረጋግጥ ግዥ በማከናወን በድምሩ ብር 1,205,293.97 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

3. በጨረታ መፈጸም ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ፣

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች በአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም

የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም ሰኔ 2002 የወጣው የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 በአዋጅና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም መንግስት የግዥ አፈጻጸም በመመሪያ መሰረት መፈጸም እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡ አስተዳደሩ በመመሪያው መሰረት እያከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ የግዥ ወጪዎች ናሙና ተወስዶ ኦዲት ሲደረግ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ በድምር ብር 5,896,037.16 የተለያዩ የዕቃ ግዥ ከመመሪያ ውጭ በማወዳደር በጨረታ ማከናወን ሲገባው በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ በመፈጸም ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

በጨረታ መገዛት ሲገባው በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ፣

በፌዴራል መንግሥት የግዥና የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 33 ቁጥር 4 በዚህ አዋጅ ወይም በግዥ መመሪያው የተዘረጉ የግዥ ስርዓቶችን ለማሻሻል የመንግስት መ/ቤቶች በአንድነት መፈጸም የሚገባቸውን የእቃ፣ የግንባታ ወይም የአገልግሎት ግዥዎችን መከፋፈል የለባቸውም ይላል፡፡ ባለስልጣኑ በመመሪያ መሰረት ተግባራዊ እያደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፡-

ባለስልጣን መ/ቤቱ ለስልጠና የሆቴል መስተንግዶ አገልግሎት ግዥ በጨረታ መፈጸም ሲገባው በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ በተደጋጋሚ በማከናወን በድምሩ ብር 4,582,912.34 ከፕሮጀክት ሂሳብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

. መመሪያ ከሚፈቅደው የብር መጠን በላይ የተፈፀሙ ግዥዎች፣

የፌዴራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ 2002 ዓ.ም አንቀጽ 24/1፣አንቀጽ 24.3 ፊደል ሀ እና ለ፣ አንቀጽ 24.12 እንደ ቅደም ተከተላቸው፡የመንግስት መ/ቤቶች አስቀድሞ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ ግዥን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው፡፡ በተጨማሪ የገንዘብ ሚኒስቴር መስከረም 25, 2014 ዓ.ም በተሻሻለው የግዥ መመሪያ ተራ ቁጥር አንድ ላይ የጥቃቅን ግዥዎች (እቅድ ውስጥ ያልተካተቱ) ለአንድ ጊዜ ግዥ ብር 10,000.00 በዓመት ከ150,000.00 ብር ያልበለጡ ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በቀጥታ ግዥ ከማናቸውም ሻጭ ድርጅት መፈጸም እንደሚችሉ

ተገልጿል፡፡ ባለስልጣኑ በዚህ መመሪያ መሠረት ግዥ የሚፈፅም መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ፣

ባለስልጣን መ/ቤቱ በበጀት ዓመቱ የተለያዩ ዕቃዎች ዕቅድ ላይ ያልተካተቱ ግዥ በሚል በመመሪያው ከተፈቀደው የብር መጠን ገደብ በላይ ያለአግባብ በድምሩ ብር 283,278.80 በቀጥታ ግዥ የተፈፀመ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

6. እርምጃ ያልተወሰደባቸው የ2013 በጀት ዓመት ኦዲት ግኝቶች

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በየበጀት ዓመቱ የባለስልጣኑ ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ባለስልጣኑ ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- በድምሩ ብር 6,882.85 ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን በኦዲት ታውቋል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት